# ጋዜጣዊ መግለጫ

አሜሪካን ኤምባሲ
አዲስ አበባ
2015/27

ለተጨማሪ መረጃ በ011-130-7033 ይደውሉ
ድረ-ገጽ - http://ethiopia.usembassy.gov

---

## *አዲስ የሽምብራ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ በአዳማ ይፋ ተደረገ*

### *አዲሱ ቴክኖሎጂ አቀናባሪዎችና ላኪዎች የኢትዮጵያን ሽምብራና የቅባት እህሎች ከፍተኛ ዋጋ ሊያወጡ ወደሚችሉበት ገበያ እንዲልኩ ያስችላቸዋል*

*ነሐሴ 19 ቀን 2007 -አዳማ፤ኦሮሚያ ክልል፤ኢትዮጵያ ፡- የአሜሪካ አለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ (ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ) እና አግሮ ፕሮም ዓለም አቀፍ በዛሬው ዕለት አዲስ የሽምብራ ማቀነባበሪያና ማበጠሪያ ፋብሪካ በኦሮሚያ ክልል በይፋ መርቀው ከፈቱ፡፡ የኢትዮጵያ ሽምብራ በጥራት መጓደል የተነሳ ብዙውን ጊዜ ዝቅተኛ ዋጋ ወደሚያስገኙ ገበያዎች ሲላክ ቆይቷል፡፡ አዲስ የተተከለው ፋብሪካ የሽምብራን የጥራት ደረጃ 99 ከመቶ በላይ ማሳደግና በአንድ ሰዓት ውስጥ 5 ሜትሪክ ቶን የማበጠር አቅም ያለው በመሆኑ ፤ አግሮ ፕሮም ዓለም አቀፍ የተባለው ድርጅት የኢትዮጵያን ሽምብራ ከፍተኛ ዋጋ በሚያስገኙ የአሜሪካ ፣ አውሮፓና መካከለኛው ምስራቅ ገበያዎች ለመሸጥ ያስችለዋል፡፡*

*የዩ ኤስ ኤ አይ ዲ የኢትዮጵያ ዳይሬክተር ዴኒስ ዌለር ባደረጉት ንግግር “በዓለም ላይ ብዙ ህዝብ ጤናማና ጣፋጭ የፋይበር እና የፕሮቲን ምንጭ የሆነው ሽምብራ ላይ ትኩረት ማድረግ ጀምሯል፡፡ የዚህ አይነቱ ማጣሪያ ፋብሪካም ብዙ ገበያዎችን ለመድረስና የኢትዮጵያ ገበሬዎች የተሻለ ገቢ እንዲኖራቸው እንደሚያደርግ ጽኑ እምነት አለን” ብለዋል፡፡*

*የማበጠሪያው ማሽን ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ የኢትዮጵያን የሽምብራ ዘርፍ ተወዳዳሪነትና እምቅ አቅም ለማሻሻል የነደፈው የግራንት ፕሮግራም ውጤት ነው፡፡* ከሽምብራ በተጨማሪ ሰሊጥ የማቀነባበር አቅም ያለው ይህ የማበጠሪያ ማሽን ፤ 765 ሺህ የአሜሪካን ዶላር ዋጋ የሚያወጣ ሲሆን ፤ ከዚህ ውስጥ ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ከ168 ሺህ የአሜሪካን ዶላር በላይ የገንዘብ ድጋፍ ያደረገ ሲሆን፤ አግሮ ፕሮም ዓለም አቀፍ ቀሪውን ወጪ ሸፍኗል፡፡

*“በሽምብራ ምርት ከአፍሪካ አንደኛ የሆነችው ኢትዮጵያ ፤ በዓለም አቀፍ ገበያም ዋና ተዋናይ መሆን ይገባታል፡፡ ገበሬዎች ከሽምብራ ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙ ከሆነ ፤ እንደ ጥራጥሬ የመሳሰሉ ዝቅተኛ ዋጋ የሚያስገኙ ምርቶች ላይ እምዛም አያተኩሩም፡፡ አግሮ ፕሮም የዓለም አቀፍ ገበያ ዋጋን ይመራል፤ አዳዲስ ዓለም አቀፍ ገዢዎችንም እንዲሁ” በማለት የአግሮ ፕሮም ዓለም አቀፍ መሥራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኤልያስ ገነቲ ተናግረዋል፡፡*

*ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ የግብርና ገበያ ልማት ዘርፍ ምርታማነትንና ተወዳዳሪነትን ለማሻሻል የሚያግዝ የተቀናጀ ስልት ይከተላል፡፡ ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ከግብርናና ከንግድ ሚኒስቴር፤ ከኅብረት ሥራ ዩኒየኖችና ከግሉ ዘርፍ ጋር የተሻሻሉ የሽምብራና የቅባት እህሎች ዝርያዎችን የተሻለ ምርት መሰብሰብያና ድህረ ምርት አያያዝ ቴክኒኮችን እንዲሁም የማቀነባበሪያና ማበጠሪያን ጨምሮ በማስተዋወቅ ረገድ በጋራ ይሰራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የአሜሪካ አለም አቀፍ የልማት ድርጅት የሽምብራና የቅባት እህሎች ላኪዎች የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኙና ከዓለም አቀፍ ገዥዎች ጋር በዓለም አቀፍ ንግድ ትርዒቶችና ኮንፍረንሶች አማካኝነት እንዲገናኙ ድጋፍ ያደርጋል፡፡*

###

*ለተጨማሪ መረጃ፡ https://www.usaid.gov/ethiopia ይመልከቱ*